የተከበራችሁ ጥሪ የተደረገላችሁ እንግዶች፤

የተከበራችሁ፤ የቀዳማዊ ኃይለ ሥለሴ ሐረር ጦር  አካዳሚ ምሩቃን ማህበር አባላትና ቤተሰቦች፤

የቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ ጦር አካዳሚ ምሩቃን ማህበር በሰሜን አሜሪካ የተመሰረተበትን 10ኛ ዓመት በምናከብርበት ምሽት ላይ ተካፋይ ለመሆን ጥሪውን አክብራችሁ በመገኘታችሁ በሥራ አስፈፃሚው ኮሚቴና በበዓል አዘጋጅ ኮሚቴው ስም እንኳን ደህና መጣችሁ እያልኩ ይህንን በጉጉት ስንጠብቀው የነበረውን ታላቅ በዓል ለማክበር ላበቃን ለልዑል እግዚአብሔር ምስጋና አቀርባለሁ።

በዚህ በዓል ላይ ለመገኘት ከልብ ተመኝተውና ጓጉተው በስራና በተለያዩ ምክንያቶች ለመምጣት ላልቻሉ ወንድሞቻችንና ቤተሰቦቻቸው በመካከላችን ባለመገኘታቸው ቅር ብንሰኝም በመንፈስ በዓሉን ከኛ ጋር እንደሚያከብሩ በመተማመን ‘ እንኳን አብሮ ደስ አለን’ እንላቸዋለን።

የቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ ሐረር ጦር አካዳሚ አርማ ላይ የነበረው “ ከራስ በፊት ለሀገር “ የሚለውን መፈክር የህይወታችን መመሪያ አድርገን መርጠን ሀገራችንና ሕዝባችንን እስከ መጨረሻዋ የደም ጠብታ መስዋዕትነት ለመክፈል በገባነው ቃል መሰረት ያበረከትነው አገልግሎት ለመዘርዘር ያስቸግራል። “ከራስ በፊት ለሀገር “ የሚለው ጉዳይ ሲነሳ በጭንቅ ሰዓት ወኔና ቆራጥነት ወደ ታች ሊንሸራተት ሲል መልሶ አቁሞ ጀግንነትንና ድፍረትን ያላብሳል። እምነት ሊጨልም ሲል እንደገና ብርሃን ፈንጥቆ ተስፋን ያጎለብታል። ለመጨረሻውና እንደገና መልሰን የማናገኘውን ብርቅ የሆነውን አንድ ህይወት በመስዋዕትነት ካለቅሬታ ለመክፈል ያዘጋጃል። ይህ ዕጹብ ድንቅ የሆነ ከራስ በፊት ሀገርን ማስቀደም የሚለው ምስጢር በእኔ አንደበት ተዘርዝሮ የሚያልቅ አይደለም። ለታሪክ ፀሃፊዎችና ለባለቅኔ ዘራፊዎች ትቼ ማለፋን እየመረጥኩ ሳልጠቅስ እማላልፈው ጉዳይ ቢኖር ግን ከላይ የጠቀስኩት መፈክር እያንዳዱን የትምህርት ቤታችን ምሩቅ የሆነ መኮንንን ቀጣይ ህይወቱን በትክክለኛው መንገድ እንዲመራ በማድረግ ጠንካራ አቋምንና መልካም ፀባይን ቀርፆለት ለሀገር ነፃነትና ሉዓላዊነት ዘብ እንዲቆም ከማድረጉ በተጨማሪ ድክመት ሲያጋጥመው በፍጥነት ድክመቱን ተረድቶ መልሶ እንዲበረታታና ጥርጣሬ በገባው ወቅት በእርጋታ አስቦ ትክክለኛውን መፍትሄ እንዲመርጥ አድርጎታል። የእውነተኛው ከአቅም በላይ የሆነው የጭንቅ ማእበል በሚደርስበትም ወቅት አቅም በቻለው ሁሉ ተፋልሞ መቋቋምንና በአሸናፊነት መውጣትን አስተምሮታል። ኩራትንና መመፃደቅን በተቻለው ሁሉ መዋጋትና ማራቅን አስገንዝቦ ለተሸነፈው ጠላት ደግሞ ርህራሄን በመሳየት ሰብአዊነት ምን ያህል ሌላው የጦርነት ገፅታና በጎ ባህል እንደሆነ ግንዛቤን አስጨብጧል። ሀገርን በውትድርና ማገልገል ሀብትና ድሎትን አያስገኝም፤ ይልቁንም ምርጫው ከባድና አስቸጋሪ የሆነ ህይወትን መርጦ ለሀገር ሲባል መንከራተትንና ብሎም የህይወት መሰዋዕትን ፅዋ በፈቃደኝነት መቅመስ ነው። ዛሬ ያን ሁሉ መከራ አልፈን በህይወት ኖረን ይህንን ምሽት ለማክበር መቻላችን  ዕድለኞች ነንና ልዑል እግዚአብሔርን ልናመሰግነው ይገባል።

የተከበራችሁ አባላትና ቤተሰብ፤
የተከበራችሁ እንግዶች፤

ዛሬ ይህን ታሪካዊ በዓል ስናከብር ምን ያህል ደስተኞች እንደሆንን መገመት አያዳግትም። ከሁላችን ፊት ላይ የሚነበበው የደስታ ገፅታ ምስክር ነው። ይሁን እንጂ በዓሉ ባለፉት 10 ዓመታት ጉዞው ውስጥ ያጋጠሙት አስደሳችና አንዳንዴም አሳዛኝ የሆኑ ጉዳዮችን መለስ ብለን እንድንቃኝ ስለሚያስገድደን፤

ሀ- ከዛሬ አስር ዐመት በፊት በዚህ በሰሜን አሜሪካ ይህንን አሉሚናይ አሶሲየሽን ከኛ ጋር ያያቋቋሙ አባላት

1- ሻምበል ዳምጠው አየለ
2- ኮሎኔል ካሣዬ ክፍሌ
3- ኮሎኔል ይግዛው አብርሃ
4- ሌ/ኮሎኔል ንጉሡ ተፈራ
5- ወ/ሮ አስቴር አበበ ( የሻለቃ ሙሉጌታ ከበደ ባለቤት )
6- ወ/ሮ አስቴር አሰፋ ( የዶ/ር ሻለቃ ዮሃንስ አባተ ባለቤት )

ለ- የአባላት ልጆች

1-ወ/ት መድሃኒት ብርሃኑ ( የሻለቃ ብርሃኑ ወልደ ተንሳይ ልጅ )
2-ወጣት ጃጋማ ለማ ( የኮሎኔል ለማ በየነ ልጅ )

እንዲሁም አካዳሚያችን ካፈራቸው 1018 ኢትዮጵያውያን መኮንኖች ውስጥ 435 መኮንኖችና፤ ከተለያዩ አፍሪቃ ሀገራት ከተመረቁት 42 መኮንኖች መካከል ቁጥራቸው በውል ያልታወቀ መኮንኖች ያካበቱትን ዕውቀትና ልምድ ከዳር ሳያደርሱ በተለያየ ምክንያት ህይወታቸው በአፍላው ተቀጭቶ ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩንን ሳናስታውስ ማለፍ ስለሌለብን፤ የተከበራችሁ አባላት፤ ቤተሰቦችና እንግዶቻችን ከመቀመጫችን ተነስተን በህሊና ፀሎት እንድናስባቸው በአክብሮት እጠይቃለሁ።

አመሰግናለሁ !

በእውነቱ ከአንድ ከፍተኛ ወታደራዊ ተቋም በተመረቁ መኮንኖች የዚህ አይነት አጠቃላይ መረዳጃ ማህበር ከእናት ሀገር ውጪ ተመስርቶ ለማየት መቻል ታላቅ የመንፈስ እርካታን የሚሰጥ ከፍተኛ ክንውን መሆኑ አያጠራጥርም። ቀደም ሲል በያንዳንዱ አባል ልብ ውስጥ ይህ ፍላጎት እየተብሰለሰለ ቆይቶ በጥቂት ግለሰቦች ተጠንስሶ በአጭር ግዜ ውስጥ በሰሜን አሜሪካ ለሚገኙ የአካዳሚ ምሩቃን ጆሮ ደርሶ ይህን ያህል ከፍተኛ ቁጥር ያለው አባላት ማሰባሰብ ተችሏል። ከዚህም በላይ በአጭር ግዜ ውስጥ ማህበሩ ያከናወናቸውን ተግባርና የደረሰበትን የታሪክ ምዕራፍ ስናጤን የዛሬውን በዓል ለወደፊቱ እድገታችን አመላካች የሆነ የማዕዘን ድንጋይ እንደሚሆን አያጠራጥርም።

ይሉቅንም ልዩ ደስታ የሚሰጠው በአባላት መካከል ያለው መፈቃቀር፤ መከባበርና መተሳሰብ ተግ ብሎ ከሚጠበቀው በላይ ሆኖ መገኘቱ ነው። ይህም የጠበቀ ግንኙነት መሠረቱ እጩ መኮንኖች ሆነን ሳለን በአንድ ላይ እንደወንድማማች በአንድ ገበታ እየበላን፤ በአንድ ጣሪያ ስር እየኖርን፤ ወታደራዊ እልህ አስጨራሽ ስልጠናውን በመረዳዳትና በከፍተኛ የቡድን ስሜት ተጋፍጠን በማለፋችን ነው። በዚህ ከባድ መከራ ውስጥ ማለፍ ወርቅ በእሳት የሚፈተነውን ያህል መፈተን በመሆኑ የተፈጠረው ጓደኝነትና ወንድማማችነት በቃላት ለማብራራት አስቸጋሪ ይሆንብኛል። በየሁለት ወሩ በምናደርገው ስብሰባችን ላይ የሚታየው ቁም ነገር ያዘለ ጨዋታ ሁሉ ያለፈውን ህይወት ትዝታ ከአሁኑ ህይወት ጋር እያዛመደና እያስታወሰ በተሀድሶ እንድንገናኝ በማድረጉ የስብሰባው ቀን መች በደረሰ እያልን እንድንናፍቅ

ማድረጉ ጉልህ ምሳሌ ነው። በመካከላችን የተፈጠረው መፈቃቀር፤ መግባባትና መተሳሰብ የትውልድ ድልድይ ሆነን ለማስተላለፍ ካለን ፅኑ እምነት አኳያ ቤተሰብን ማስተዋወቅ የተጀመረ ሲሆን እዚህ ላይ ሳልጠቅስ እማላልፈው በማህበሩ አባላት ቤተሰብ መካከል ድንቅ የሆነ ክስተት ማስከተሉ ነው። ይህም አባላት ያፈረቻው ልጆች በጋብቻ ለመተሳሰር በቅተው ዛሬ ወላጆቻቸውን ለአያትነት አብቅተዋል። ይህ ግንኙነት ለነገው ጥሪ መሰረት የጣለ ሂደት መሆኑን አባላት ሁሉ ልንገነዘብ ይገባል። ዛሬ ትልቁ ዛፍ ከስሩ ተቆርጦ ፍሬ ማፍራት ባቆመበት ዘመን ለአካዳሚውና ለአካዳሚው ምሩቃን ቋሚ መታሰቢያ አኖርን ለማለት የምንችልበት አንዱ ዘዴ ይህ ስለሆነ በቤተሰብ መካከል የተጀመረው ትውውቅና ትስስር የዘመን አጥር እንዳይከፍለን ስለሚረዳን ተግተን መጣር ይኖርብናል።

ለማህበራችን ምስረታ በፍጥነት ለመሰባሰብም ሆነ ለአመርቂው እንቅስቃሴውና ውጤቱ የጎላ አስተዋፅኦ ያደረገው፤ ማህበሩ ከማንኛውም የፖለቲካ እንቅስቃሴ ነፃ መሆኑን በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ አንቀፅ 7 ቁጥር 2 ላይ ህግ ሆኖ በመፅደቁና ማህበሩ የተቋቋመበት ዓላማ ላይ በፅናት መቆየታችን እንደሆነ ለማስገነዘብ እወዳለሁ።

በተጨማሪም ለማህበራችን ጥንካሬ አስተዋዕዖ አድርጓል ብለን የምናምነው አካዳሚው ካስመረቃቸው መኮንኖች ከአንደኛ ኮርስ ጀምሮ ትምህርት ቤቱ እስከተዘጋበት እስከ ሃያ አንደኛ ኮርስ ድረስ ያሉትን ምሩቃን በውስጡ አቅፎ መገኘቱ ነው። ይህም ስብስብ በዕውቀትና በረጅም አመት የሥራ ልምድ የበሰሉ ወታደራዊ መኮንኖችን እንዲያገኝ ስለረዳው ሂደቱ ሊሰምር ችሏል።

እንደምታውቁት የቀ/ኃይለ ስላሴ ሐረር የጦር አካዳሚ አገልግሎት መስጠት ከጀመረበት ግዜ አንስቶ እስከተዘጋበት ግዜ ድረስ ከተለያዬ የአፍሪቃ ሀገሮች ተቀብሎ ካሰለጠናቸው ጭምር 1221 መኮንኖች አፍርቷል። ከነዚህ ምሩቃን ውስጥ በሰለጠኑበት ሙያም ሆነ ከሙያቸው ውጭ በተለያየ የስራ መስክ እንዲሁም በአየር ኃይልና በባህር ኃይል ልዩ ልዩ ክፍሎች በመሰማራት ከ 95% በላይ የሚሆኑት ምድብ ስራቸውን በብቃት በመወጣት አኩሪ ውጤት በማስመዝገብ ለሃገራችንና ለትምህርት ቤቱ ትልቅ ስም አትርፈዋል። ከተለያዩ አፍሪቃ ሀገሮች አካዳሚው ካሰለጠናቸው ውስጥ ለምሳሌ ያህል ከናይጄሪያ ሰለጠኞች ውስጥ የ6ኛ ኮርስ ተወዳዳሪዎች ሀገራቸው ከተመለሱ በህዋላ ማህበር አቋቁመው በከፈቱት ድህረ ገፅ ላይ የደረሱበትን ከፍተኛ ማዕረግና ለሀገራቸው ያበረከቱትን አገልግሎት በመፅሔታችን ላይ ስላቀረብነው እንድትመለከቱት እጋብዛለሁ። ይህ በጣም አድርጎ ሊያኮራን ይገባል። በእርግጥ በዚች አጭር ግዜ ውስጥ ስለጦር አካዳሚውና ስላፈራቸው መኮንኖች ገድል በመናገር የዛሬውን በዓላችን ግዜ ለመሻማት ባልፈልግም በደርግ ዘመነ መንግስት ከፍተኛውን የህብረተሰብዓዊት ኢትዮጵያ የጀግና ሜዳልያን የተሸለሙት አንድ መኮንን ከምድር ኃይልና አንድ ሌላ መኮንን ከአየር ኃይል ሲሆኑ እነኚህ ጀግኖች ከዚሁ የጦር አካዳሚ አብራክ የወጡ መሆናቸውን ስገልፅ በታላቅ ኩራት ነው።

በመተዳደሪያ ደንባችን አንቀጽ 2 ላይ የማህበሩ አምስት ዓላማዎች እንዳሉት ተገልጿል። ከነኚህም መካከል በአንቀጽ 2 ቁጥር 2 ላይ እንደተገለጸው ሀገራችን ኢትዮጵያንና ህዝቦችዋ ካሉበት ችግርና ኋላ ቀርነት ለማላቀቅ እንዴት አድርገን መርዳት እንዳለብን አንስተን ብንወያይ በወደድን ነበር። ዳሩ ግን ለዚህ ሁሉ ራሱን የቻለ መድረክና ግዜ መስጠት የሚያሻው በመሆኑ ፤ ይህን ለመሳሰሉት ቁም ነገሮች ሁሉ ወደፊት በሰፊው አቅደን በድህረ ገፃችን እንገልጻለን። ሆኖም ማህበራችን ለሀገርና ለሕዝቦቻችን ያደረገውን እርዳታ የዛሬ በዓላችንን ምክንያት በማድረግ ባሳተምነው መፅሔት ውስጥ በዝርዝር ተዘግቦ ስለሚገኝ እንድታነቡት እየጋበዝኩ ማህበራችን በደስታና በሀዘን ግዜ ለአባላቱ ያደረገውን የገንዘብ

መዋጮ በአጠቃላይ መልኩ ሲታይ ማህበሩ $40,469 ሲያዋጣ አባላት ደገሞ በግላቸው $56,105 ያዋጡ ሲሆን አጠቃላይ ድምሩ $96,574 ይሆናል።

ስለ ድህረ ገፃችን ካነሳሁ ዘንድ አንድ ሳልጠቅስ የማላልፈው ጉዳይ አለ። እንደምታውቁት የትምህርት ቤታችን ምሩቃን በተለያዩ ዓለማችን ላይ ባሉ ሀገሮች ውስጥ ይኖራሉ። ይህንን እውነታ አስቀድመው በመረዳት እርስ በርሳችን ልንገናኝበትና መረጃዎችን ልንለዋወጥበት የምንችልበት ዘዴ ሊኖረን እንደሚገባ በማሰብ፤ በራሳቸው ተነሳሽነት ገንዘባቸውንና ጉልበታቸውን መስዋዕት በማድረግ ከላይ የጠቀስኩትን የማህበሩን ድህረ ገፅ የከፈቱልንን ዶክተር ሽመልስ ዓለማየሁን ሳላመሰግን ማለፍ የለብኝም። ከዚህም በላይ አሉሚናዩ በሁለት እግሩ እስኪቆም ድረስ በተደጋጋሚ ወርሃዊ ስብሰባዎች በቤታቸው እንዲኪያሄድ አድርገዋል።

ይህ ድህረ ገፃችን ከተከፈተ በህዋላ ጉልህ እንቅስቃሴ እንዲያደርግ ከዕውቀታቸው በተጨማሪ ግዜና ንዋያቸውን መስዕዋት በማድረግ ቤተሰባቸውን ጭምር በማሳተፍ ባለውለታችን የሆኑትን የመ/አለቃ ከፍያለው ሞገስን በፊታችሁ ማመስገን እወዳለሁ። በቅርብ ግዜ ደግሞ የማህበሩን ድህረ ገፅ ለማሳደግና ለማሻሻል በማሰብ ዶክተር ጌታቸው መብራቴ ባለ ሙያ ስለቀረቡ ፤ ከመቶ አለቃ ከፍያለው ሞገስ ጋር በመሆን ፤ የመሻሻሉ ተግባር በአሁኑ ግዜ እየተካሄደ ነው።

በአጠቃላይ አባላት የሆናችሁ ሁሉ ለማህበራችን የምታደርጉት በጎ ተግባርና ያላሰለሰ ጥረት በቀላሉ የሚታይ አይደለም። ምንም እንኳን እናንተ ለራሳችሁ ቤት እንዳደረጋችሁ ብትቆጥሩትም ካለባችሁ የስራ ውጥረትና የኑሮ ሩጫ የተረፈቻችሁን ሰዓትና ጉልበታችሁን መስዕዋት በማድረግ አሶሲየሽኑን ለዚህ አሁን ላለበት ስኬታማ ውጤትና አመርቂ ደረጃ አድርሳችሁታል። ከላይ ስማቸውን የጠቀስኳቸው ሁለት የህክምና ባለሙያዎች ዶክተር ጌታቸው መብራቴና ዶክተር ሽመልስ ዓለማየሁ ለአባላትና ለዘመዶቻቸው ጭምር ከክፍያ ነፃ የሆነ የህክምና እርዳታ በመስጠት ለዋሉልን ውለታ ከልብ የመነጨ ምስጋና በአባላትና በአባላት ቤተሰብ ስም እያቀረብኩ በተጨማሪም ይህ በዓል እንዲሳካ ከግል ኪሳቸው ወጪ በማድረግ የሙዚቃ ባንድና የቪድዮ ምስል ቀራጭ በማቅረብ ስለረዱን በድጋሚ ሁለቱን ሐኪሞች ላመሰግናቸው እወዳለሁ። በሀዘናችን ግዜ ከጎናችን በመሆን የምናካሂደው የቀብር ስነስርዓታችን የወታደራዊ ስነስርዓት እንዲይዝ የረዱንን የመ/አለቃ አያልነህ ደሴ ላበረከቱት አስተዋጽኦ አመሰግናቸዋለሁ። በዚህ አጋጣሚ ማህበራችንን ከመሰረቱት ትጉህ አባላት መካከል ኮሎኔል ገበየሁ ዑስማን ለረጅም አመታት በፀሀፊነት በማገልገል ላበረከቱት አስተዋጽኦ ሳላመሰግን አላልፍም። የማህበራችንን አንደኛ አመት ስናከብር የኮሚቴው ኃላፊ ሆነው በዓሉ በደመቀ ስርዐት እንዲከበር ከኮሚቴው አባላት ጋር በመሆን ለረዱን ለብ/ጄነራል ፀጋዬ ሀብትህ ይመርና እንዲሁም በዓሉ በሙዚቃ እንዲደምቅ ላደረጉት ለእጩ መኮንን መሳይ አንዳርጌ በማህበሩ ስም ምስጋናዬን አቀርባለሁ። እንዲሁም በራሳቸው ተነሳሽነት ትምህርት ሰጪ፤ ታሪክ ነክና አዝናኝ የሆኑ መልዕክቶችን ለአባላት በኢሜይል አድራሻቸው በመላክና እንዲሁም በድህረ ገፃችን ላይ የተለያዩ ፅሁፎችን በማበርከት ጥረት እያደረጉ ያሉትንና ዛሬ የበዓሉ ፕሮግራም መሪ ሆነው የሚያገለግሉንን አባልችንን ኮሎኔል ለማ በየነን እንዳመሰግን ይፈቀድልኝ። በተጨማሪም የዛሬው በዓላችንን ምክንያት በማድረግ ለህትመት የበቃውን መፅሔታችንን በተመለከተ ጉልህ አስተዋፅዖና ከፍተኛ ጥረት ያደረጉትን ኮሎኔል ለማ በየነንና ሌ/ ኮሎኔል አደፍርስ ታፈሰን እያመሰገንኩ እነኚህ መኮንኖች ለመፅሔቱ ከአባላት የቀረቡትን ፅሁፎች ታይፕ በማድረግ ማህበራችንን ከከፍተኛ የገንዘብ ወጪ እንዳዳኑት ሳልገልፅ አላልፍም። እንዲሁም የዚህ በዓል አከባበር ተጨማሪ ድምቀት እንዲያገኝ ፦

1ኛ- ለአባላት የሚሰጥ ፐላክ በማዘጋጀትና በማስቀረፅ
2ኛ- ለአባላት የሚሰጥ የምስጋና ማረጋገጫ ሰርተፊኬት በማዘጋጀትና በማሳተም፤
3ኛ- ለበአላችን የሚያገለግሉ 250 የጥሪ ካርዶችን በነፃ እንዲዘጋጅ በማድረግ፤
4ኛ- የአካዳሚው አርማ ያለበት ደረት ላይ የሚለጠፉ 500 ጌጦች በማሰራት የተባበሩንን
ዘማሪ ቢንያም ገብረ ወልድን፤
እንዲሁም አቶ አቤል ጋሼ ይህንን ፅሁፍ ከእንግሊዝኛ ወደ አማርኛ በመተርጎም ላደረጉት
አስተዋፅኦ በማህበሩ ስም ከፍተኛ ምስጋናዬን አቀርባለሁ። በአጠቃላይ ለሁሉ አባላት ከፍ ያለ
ምስጋናዬን እያቀረብኩ እንግዶችም ጭምር በጭብጨባ እንድታጅቡኝ እጠይቃለሁ።

በአጠቃላይ ለሁሉ አባላት ከፍ ያለ ምስጋናዬን እያቀረብኩ እንግዶችም ጭምር በጭብጨባ
እንድታጅቡኝ እጠይቃለሁ።

አመሰግናለሁ !

እንደሚታውቀው የማህበራችን ቁም ነገሩ መቋቋሙ ብቻ ሳይሆን ከመቋቋሙ የበለጠ የሚከብደውና የየአንዳዱን አባል ቁርጠኛነት የሚጠይቀው፤ የተቋቋመው ማህበር ዕድገት ሳይደናቀፍ እየጎለበተ እንዲሄድ በወንድማማችነት ዐይን የምንቀራኝበት ገመድ እንዳይረግብ አጥብቆ ከመያዙ ላይ ነው። የዚህ ማህበር ህልውና የሚጠበቀው እያንዳዱ አባል በሚያሳየው የመንፈስ ቅንነት፤ራስን መግዛትና ቆራጥነት እንዲሁም የቡድን መንፈስ ማጎልመስ ሲሆን እርስ በርሳችን የምናሳየው ፍቅር ደግሞ ከራሳችን አልፎ ለሀገርና ለወገን ጭምር ጠቃሚ እንደሚሆን አያጠራጥርም። ትልቁ ቁም ነገር ሁሉም ሊረዳው የሚያስፈልገውና ቤተሰብንም ጭምር አደራ የምንለው፤ ይህ ማህበር ከልብ መሻታችንን ተመልክቶ እግዚአብሔር በፈቀደው ግዜ ያቋቋመው በመሆኑ ሁላችንም በትግስትና በእርቆ አስተዋይነት ልንጠብቀው የሚገባ መሆኑን ነው። ለትውልድ እንዲተላለፍ ሳናደርግ ቀርተን በልጆቻችን ተወቃሽ ላለመሆን እርቀን ማስተዋል ይኖርብናል። ዕንቅፋቶች አያጋጥሙም ብሎ ማሰብ አይቻልም። ግን ችግሮች በቀላሉ መፍትሄ እንዲያገኙ በታኝ የሆኑ እንቅፋቶችን ቀድሞ በንቃት በመጠበቅና በመከላከል፤ የሚሰማንን በግልጽ በመወያየት ለሀሜት ሳንጋለጥ በፅናት ጠንክሮ መቆም ያስፈልጋል። የአንድ ትምህርት ቤት ልጆች በመሆናችን ለመግባባትና ለመተሳሰብ ከፍተኛ እድል አለን። በእርግጥ እስካሁን የሚታየው ሁሉ ይህንን የሚመሰክር በመሆኑ የስራ አስፈፃሚው ኮሚቴው በጣም ደስተኛ ነው። ወደፊትም ብዙ ስራ ስለሚጠብቀን ይህ ጠንካራ መንፈስ ዘላቂ እንዲሆን መጣር፤ መጣር አሁንም አበክሮ መጣር ያስፈልጋል።

የተከበራችሁ ውድ አባላትና ቤተሰብ
የተከበራችሁ ውድ እንግዶቻችን !

ይህ ማህበር በያንዳንዱ አባል ንቁ ተሳትፎ በዚህ በአጭር ግዜ ውስጥ ባሳየው ፈጣን እድገት እስካሁን ያከናወናቸውን ለእንግዶቻችን ማስጨበጡ ተገቢ ስለሚመስለኝ እንደሚከተለው በአጭሩ አቀርባለሁ፦

1- ህጋዊ ሰውነት አግኝቷል። ይህ ማህበር በዚህ አገር መንግስት ህጋዊነት ማግኘቱ እጅግ ጠቃሚ ስለሚሆን ምናልባት ለሚያጋጥሙት ህግ ነክ ጉዳዮች ሁሉ ለሚመለከተው የመንግስት አካል አቅርቦ ለማስፈጸም ከመርዳቱም በላይ በአገሪትዋ ውስጥ ካሉ የዕርዳታ ተቋማት ጋር ለማነጋገርና አንዳንድ ለወገን የሚጠቅም ስራዎች ለመስራት ተቀባይነት ያስገኝለታል።

2 - ድህረ ገፅ ከፍቷል። ድህረ ገፅ መክፈቱም ቀደም ብዬ እንደገለፅኩት በጣም መጠነ ሰፊ አገልግሎት እንደሚሰጠን ግልፅ ነው። በዚህም ላይ ማህበራችን ከዘመኑ ቴክኖሎጂ ጋር መቆራኘቱ ለልጆቻችን ስለ ትምህርት ቤታችንና ግንኙነታችን በቀላሉ ለማስረዳት ያመቸናል።

3 - ቢሮ ከፍቷል ፤ማህተምም አሰርቷል። የቢሮውና የማህተሙ ጉዳይ ለማንናውም አስተዳደራዊ ጉዳያችን ስርዐት የተከተለ አሰራር ለመስራት ጠቃሚ መሳሪያ እንደሚሆነን ለናንተ መንገር አያሻም።

ቀደም ሲል ተቋቁሞ የነበረው  የኢንቬስትመንት ኮሚቴ  ከእያንዳንዱ  አባል በነፍስ ወከፍ $ 2000 አሰባስቦ  ሥራ ከመጀመሩ በፊት በሙያው ዕውቀት ያላቸውን ሁለት ግለሰቦች ምክር እንዲያካፍሉን ጋብዞ አወያይቶ ነበር። ከባለሙያዎቹ የተገኘው ምክር ግን በተሰበሰበው መዋጮ የረባ ኢንቤስትመንት ለማከናወን እርባና የሌለው መሆኑን ገልፀው ከአባላት አማካኝ እድሜም አኳያ ሲታይ ኢንቤስትመንቱ የሚያስገኘውን ንዋይ ለመቋደስ ተስፋው የጨለመ መሆኑን ማስደመጣቸው የምናስታውሰው ጉዳይ ይመስለኛል። አባላትም ቸኩለን ተስፋ በመቁረጥ የተሰበሰበው ገንዘብ መዋጮ ለከፈሉት አባላት እንዲመለስ አድርገናል። ዛሬ ወደህዋላ ተመልሰን ስናየው የተሰበሰበውን ገንዘብ ቋሚ ንብረት ላይ አውለነው ቢሆን ኖሮ ምን ያህል ተጠቃሚዎች እንሆን እንደነበር መገመቱ አስቸጋሪ አይደለም። ላለፈው ክረምት ቤት አይሰራምና ያለፈውን ስህተታችንን በትምህርት ሰጪነቱ ተቀብለን ዘላቂና ለጡረታ ጭምር የሚያገለግል መንገድ መፈለግና መጣር እንደሚገባን ላሳስብ እወዳለሁ።

እንደምታዩት ግዚያዊ የበዓል አዘጋጅ ኮሚቴም አዋቅረን ዛሬ ይህንን የመሰለ የተዋጣለት ዝግጅት አቅርበውልናል። የኮሚቴው ኃላፊ ሻለቃ ሚካኤል ዘወልደንና የቀሩትንም የኮሚቴው አባላትን ከልብ እያመሰገንኩ  በመጨረሻም መ/አለቃ ዮናስ በዓሉ የተሳካ እንዲሆን ላድርጉት ከፍተና እርዳታና ትብብር  ከልብ አመሰግናቸዋለሁ።

በመጨረሻም  በዝግጅቱ ላይ ለተሳተፋችሁ አባላት ሁሉ ልባዊ ምስጋናዬን እያቀረብኩ በዓሉ የደስታና የሰላም እንዲሆንና እግዚአብሄርም እንዲባርከው እመኛለሁ።

አመሰግናለሁ !